# የጎዳሴ ግድብ



ይታያል ከሩቁ ኣድማሱ ደም መስሏል፣
ጨለማው ኣብቅቷል፣ ሌሊቱም ነግቷል
ዕልል! ዕልል! በሉ ዕድላችን ፈክቷል፣
ደኑ ተመንጥሮ፣ መሰረት ተጥሏል፣
ጉም፣ ዳመናው በንኖ ብርሃኑም በርቷል።
ለሥራ እንነሳ፣ ለዕድገታችን ነው
በሥራ መበርታት ደግ ነው! ደግ ነው!

ጠላቶቻችንን ድህነት፣ ስንፍና፣
ታላቁ ጠላትም ኣቶ ድንቁርና
ኋላ ቀርነትን ያስከትላልና. . .
ሌሊቱ ኣበቃ፣ ጎሕ ቀድዷል ሰማዩ፣
የሥራ ሰዓት ነው ደምቋል ፀሓዩ።
ተነሱ፣ እንነሳ ዛሬ ዘመኑ ነው
ለሥራ እንነሳ፣ ሥራ እኮ ክብር ነው፣
ለሰላም መነሳት ደግ ነው፣ ደግ ነው!



በትጋት ለመሥራት ዓላማችንን
በኣንድነት ታጥቀን ትግላችንን
ምንም ሳንታክት እንቆማለን
ቅድመ ኣያቶቻችን ከጥንቱ ሲምሉ
“ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ” ሲሉ
ተፈጽሟል ዛሬ ትንቢቱ በሙሉ
ለሥራ ተነሱ፣ ሥራ እኮ ክብር ነው፣
ለሰላም መነሳት ደግ ነው፣ ደግ ነው!



ሩቅና ቅርብ ያሉት ጠላቶቻችን
መቸም ኣይተኙልን ምን ጊዜም ቢሆን
ኣምላክ በጥበቡ ሰርክ ሲጠብቀን
የጠላቶቻችን ውድቀት ኣሳየን
ተከናንበው ውርደት፣ ተሸክመው ውርደት
ሁሉም ተንኮታኩተው ኣለቁ በኣንድነት
ለሰላም መነሳት ደግ ነው፣ ደግ ነው. . .
ወገኔ እንዳትሞኝ እንትንህን ደግነው!

ገ/ኢ. ጐርፉ።